# የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

# የተሸከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ

መመሪያ ቁጥር፡ 821/2013

## ግንቦት 2009 ዓ.ም

## አዲስ አበባ

ክፍል አንድ፡

## ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚር ባወጣው የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት አድርጎ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም -

- 3.1 "የበላይ ኃላፊ" ማለት ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ማለት ነው፡
- 3.2 "ኢንስቲትዩት" ማለት ዋና መስሪያቤትን ጨምሮ በሥሩ የሚገኙ የምርምር ማዕከላትን የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማለት ነው፡
- 3.3 "ኃላፊዎች" በኢንስቲትዩቱ ዉስጥ የሚገኙ የስራ ሂደት ዳይሬክተሮች እና የማዕከል ዳይሬክተሮች ማለት ነው፡
- 3.4 "ተሽከርካሪ" ማለት በመንገድ ላይ በሞተር የሚንቀሳቀስ ወይም የሚጎተት ለሰው ወይም ለዕቃ ማጓጓዣ የሚውል ማንኛውም ተሽከርካሪ ማለት ነው፡
- 3.5 "ልዩ መታወቂያ" ማለት የኢንስቲትዩቱን ተሽከርካሪዎች ለሚያሽከረክሩ ኃላፊዎች የኢንስቲትዩቱን ተሽከርካሪ ለማሽከርከር የተፈቀደላቸው መሆኑን ለሚረጋገጥ የሚሰጥ የመታወቂያ ካርድ ነው፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ውጭ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ፣ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ባካተተ አሠራር የተጠቃሚዎችን ፍላጎት በሚካት የኢንስቲትዩቱን ተልዕኮ እንዲሳካ ለማድረግ ነው፡፡

## 5. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በዋናው ማቤትና በኢንስቲትዩቱ ስር በሚኙ ሁሉም ማእከላት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ፩. የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ ሚጃ አያያዝ፤ ስምሪት፤ አጠቃቀምና ቁጥጥር

### ፩.1 የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ ሚጃ አያያዝ

፩.1.1 ኢንስቲትዩቱ በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር፣ በኪራይና በሌሎች መሰል ማገዶች ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉትን ሚጃዎች ማዞገቦ ይይዛል፡፡

ሀ) የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር፣ አይነትና ሞዴል

ለ) የጭነቱ ልክ (በሰው፣ በኩንታል፣ በኪዩቢክ ሜትር፣ በሊትር)

ሐ) የቻንሲና የሞተር ቁጥሮች

መ) የሚጠቀመው የነዳጅ ዓይነት

ሠ) የተገዛበት ወይም በማቤቱ ባለቤትነት ስር የዋለበት ቀንና ዓመተ ምህረት

ረ) ተሽከርካሪው የተገኘበት ሁኔታ -በግዥ፤ በስጦታ፤ በርዳታ ወዘተ…

ሰ) የተሽከርካሪው ዋጋ

ሸ) የባለቤትነት ማቃወቂያ ደብተር

፩.1.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት ሚጃዎች በበቂ ምክንያት ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ባሉት ሚጃዎች መሰረት ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ ያልተገኙትን

ሚጀዎች ዝርዝርና ምክንያት በተሽከርካሪው የህይወት ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ ይያዛል፡፡ ያልተሟላትንም ሚጀዎች እንዲሟሉ ጥረት ይደረጋል፡፡

፩.1.3 እያንዳንዱ የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ ማዘገብ የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስከወገድ ድረስ በኪ/ሜ የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ የተጓዘው ኪ/ሜ መጠን በማን ይዞታ ስር እንደነበረ ወዘተ አካቶ መያዝ አለበት፡፡

፩.1.4 የተሽከርካሪው የህይወት ታሪክ ማዘገብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እየተፈተሸ ወቅታዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

፩.1.5 ሚጀ አያያዙ ዘመናዊ የሆነ ና በኢንፎርሜሽን ቴክኖለጂ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡

## ፩.፪. የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ ስምሪት

በኢንስቲትዩቱ ዋናው መስሪያ ቤትና በማዕከላት ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች ለመስክ ጉዞ፣ ለከተማ ውስጥ ሥራና ለሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ተለይተው ይደለደላሉ፡

፩.፪.1 ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት ለመጠቀም እንዲያስችል ስምሪታቸው በፑል ይሆናል፤ የሥራ ሂደቶች የስምሪት ጥያቄው በየሥራ ሂደቱ ተቀናጅቶ ይቀርባል፡፡ በዚህ መሠረት የቀጣዩ ወር የመስክ እንቅስቃሴና የተሽከርካሪ ጥያቄ ወሩ ከመድረሱ ከ ፯ (ሰባት) ቀናት በፊት ለትራንስፖርት ስምሪት ይቀርባል፡፡

፩.፪.፪ ለድንገተኛ የመስክ ሥራዎች የተሽከርካሪ አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ ካለው አቅርቦት ጋር በማመጣጠን የኢንስቲትዩቱ አስተዳደርና አቅም ግንባታ ምዋና ዳይሬክተር ወይም ውክልና የተሰተው ክፍል አስቸኳይነቱን ገምግሞ ጥያቄው እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡

፩.፪.3 ለማንኛውም የተፈቀደ የመስክ ጉዞ ተሽከርካሪ ለማስሜራት በትራንስፖርት ስምሪትና ጥገና በድን የተፈረመ የመንግስት የተሽከርካሪዎች አገልግሎት መጠየቂያና ማዘዋወሪያ ቅፅ መያዝ አለበት፡፡

፩.፪.4 የሥራ ሂደቶች/ ሠራተኞች የከተማ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲፈልጉ የተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅፅ ተሞልቶና በሚመለከተው የሥራ ሂደት

ኃላፊ ተፈቅዶ ለትራንስፖርት ሥምሪት በድን ከቀረበ በኋላ አገልግሎቱ የሚሰጠው በቅደም ተከተልና በማቀናጀት ይሆናል፡፡

፩.፪.5 ለከተማ ውስጥ አገልግሎት የተመደቡ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ጥገና ሲገቡና ሌላ ተመጣጣኝ ተሽከርካሪ መመደብ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ለመስክ ስራ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች በትራንስፖርት ሥምሪትና ጥገና በድን አማካኝነት በከተማ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል፡፡

፩.፪.፮ አሽከርካሪዎች ከመስክ ጉዞ ሲመለሱ በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት አፈጻጸማቸውን ለትራንስፖርት ሥምሪት በድን ሪፖርት ያደርጋሉ፤

፩.፪.፯ ለኃላፊዎች የተደለደሉ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ለጥገና ወደ ጋራዥ ሲገቡ አቅርቦቱና የስራው ባህሪ እየታየ አነስተኛ ተሽከርካሪ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፩.፪.፰ በግል ተሽከርካሪ የተመደበላቸው ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በዓመት ፈቃድ እንዲሁም ከአንድ ወር በላይ በሚሰጥ ሥልጠና ምክንያት በሚኖሩበት ጊዜ ተሽከርካሪውን ለትራንስፖርት ሥምሪትና ጥገና በድን ማስረከብ አለባቸው፡፡

፩.፪.፱ በግል ተሽከርካሪ የተመደበላቸው ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በበላይ ኃላፊ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ከ45 ኪ/ሜ በላይ ማሽከርከር አይችሉም፡፡

፩.፪.10 የሥራ ሂደት ዳይሬክቶሬቶች የቀጣዩን ሳምንት የከተማ ውስጥ የተሽከርካሪ ጥያቄአቸውን ዘወትር አርብ እስከ ቀኑ 5፡00 ሰዓት ድረስ ለትራንስፖርት ስምሪትና ጥገና በድን ያቀርባሉ፡፡ የትራንስፖርት ስምሪት በድንም የቀረበለትን ጥያቄ በማቀናጀት ፕሮግራም ያወጣል፤ ለጠያቂው ያሳውቃል፡፡ ሆኖም በሚከሰት የሚከለሱን ዳይሬክተር በማፅደቅ ዘወትር ሰኞ እስከ ጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው የሥራ ሂደት ወይም በድን ያሳውቃል፡፡

፩.፪.11 የትራንስፖርት ስምሪት ባለሙያው በቀረበው ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ የተሽከርካሪ ጥያቄ መሠረት በተሽከርካሪዎች ማዘዋወሪያ ቅጽና በበር የይለፍ ፈቃድ ላይ ማሻ ከሎሜትርን ጨምሮ በመመዝገብ እየፈረመበት አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፩.፪.1፪ የስምሪት ባለሞያው የቀረበለትን የተሽከርካሪ ስምሪት ጥያቄዎችለማቅናጀት ችግር ካጋጠመው ከሚመለከታቸው የሥራ ሂደት ዳይሬክተሮች/ከማእከልከዳይሬክተሩ ጋር በመወያየት ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡

፩.፪.13 ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በቀር የተሽከርካሪዎችን አያያዝ ወጥነት ለማድረግ ለአንድ ተሽከርካሪ አንድ ሾፌር እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፩.፪.14 ኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ የሚመደበው ባለው አቅም ነው፡፡ ሆኖም ከሥራው አስፈላጊነት አንጻር የተሽከርካሪ ዕጥረት ሲያጋጥም በጀት መኖሩን በሚያጋጥ የማግስት የአገልግሎት ግዢን ደምበና መመሪያ በመከተል ተሽከርካሪበመከራየት አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## ፩.3. በሁኔታዎች አስገዳጅነት ከዕቅድ ዉጪ የሚቀርቡ የተሽከርካሪ አገልግሎት ጥያቄዎችን ስለማስተናገድ

**፩.3.1 ለከተማ ስምሪት፡-** በዋናው ማዕከት በሥራ ሂደት ዳይሬክተሮች፣ በማእከላት በማእከሉ ዳይሬክተር ሲፈቀድ፣

**፩.3.፪ ለመስክ ስምሪት፡-** በዋናው ማዕከት በበላይ ኃላፊው፣ በማእከላት በማእከሉ ዳይሬክተር ሲፈቀድ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

- በመስክ ጉዞ ላይ አሽከርካሪው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥመው ለትራንስፖርት ስምሪትና ጥገና ቡድን አስተባባሪ በማሳወቅ ተገቢው የመንጃ ፈቃድ ደረጃ ያለው ተጓዥ እስከ ሚቀጥለው ከተማ ድረስ ብቻ እንዲያሽከረክር ይፈቅዳል፣
- የሠራተኛ መጓጓዣ ሰርቪስ መኪና በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎቱ በቋረጥ ከሌለ ማእከል በወቅት ወይንም ከሌላ ድርጅት በኪራይ አገልግሎቱን እንዲያገኙ የስምሪት ባለሞያው ከትራንስፖርት ተ/ጥ/ዳይሬክተሩ ጋር በመነጋገር እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡ ሆኖም የተጠቀሰው አማራጭ ሳይሳካ ቢቀር ሠራተኛው በራሱ ትራንስፖርት በመጠቀም በሥራው ላይ እንዲገኝ ያሳውቃል፣

- ለጉዞ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ማጠናቀቅ ያልቻሉ የመስክ ሥራዎች ሲያጋጥሙማጠናቀቅ የሚያስችል ተጨማሪ ቀናት በበጀት ሚዛን ለሥራ ሂደት ዳይሬክተር ወይም ለማዕከል ዳይሬክተር አሳውቆ ማስፈቀድ ይችላል፣

## ክፍል ሶስት

### ፫. ስለ ተሽከርካሪ ደልደላና የትራንስፖርት አበል አከፋፈል

### ፫.፩. በግል ስለሚመደብ ተሽከርካሪ

በኢንስቲትዩትደረጃ የሚገኙ ሁሉም የምርምርና የድጋፍ ሰጭ ዳይሬክተሮችና የማዕከል ዳይሬክተሮች ልዩ የተሽከርካሪ አገልግሎት እንደሚያስፈልጋቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የስራ ኃላፊነትንና ባህሪን ባገናዘበ መልኩ ከዚህ በታች በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሰረት የተሽከርካሪ ደልደሉ በበላይ አመራሩ እየታየ ይወሰናል፡፡

በዋናው መስሪያ ቤት

- ለምርምር ዳይሬክተሮች፤
- ለቴክኒክ ድጋፍ ሰጭዳይሬክተሮች፤
- ለአስተዳደር ድጋፍ ሰጭዳይሬክተሮችና ባለሙያዎች (ፕሮቶኮልና ኢንሹራንስ)፤

በማዕከል

- የማዕከል ዳይሬክተሮች፤፣ በማዕከል የሚገኙ የምርምር ዳይሬክተሮች

### ፫.፪. የትራንስፖርት አበል አከፋፈልና የነዳጅ ደልደላ

ኢንስቲትዩቱ በተሽከርካሪ ወጻንነት ከላይ ለተገለፀት የሥራ ኃላፊዎች በሙሉ ተሽከርካሪ ሟልደል የሚይቻል ሆኖ ሲገኝና እንዲሁም ያሉትን ተሽከርካሪዎች ዕድሜ በሚዞም በቁጠበ ለማጠቀም እንዲቻል የትራንስፖርት አበል እንዲከፈላቸው ይደረጋል፡፡ የአበሉ ተመኅ አመዳደብ ተሽከርካሪ በምድብ ለወጣ የሚችለወን የተሽከርካሪ ዉጪ /የነዳጅ፣ ዘይት፣ የቅባት፣ የጥገናና ..ወዘተ/ በማገናዘብ ነው፡፡ በመሆኑም -

ሀ) የምርምርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪየስራ ሂደት ዳይሬክተር/ማከል ዳይሬክተር

የስራ መዎች፣ የተመራማሪዎችና የቴክኒክ/ላቦራቶሪ ረዳቶች የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ በማስመልከት ከጠቅላይ ሚር ጽ/ቤት በተፈቀደወና ከሲቪል ሰርቪስ ሚር ሰኔ 13 ቀን 2006 ዓ.ም. በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 13.1/ጠ10/10/226 በተጻፈ ደብዳቤ በተላከው የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ተፈጻሚይሆናል፡፡

ለ) የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪየስራ ሂደት ዳይሬክተር

ተሽከርካሪ ለምደብለት ላልቻለ የድጋፍ ሰጪ የሥራ ሂደት ዳይሬክተር ስለሚከፈለው የትራንስፖርት አበል በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ ማቤቶች ግልጽ መመሪያ ለተቋመሲደርስ የሚጸም ይሆናል፡፡

ሐ) የነዳጅ ደልደል

ተሽከርካሪ በግል ለተመደበለት ኃላፊ/ ባለሞ

- ቤንዚን በወር 160 ሊትር እንዲሁም ናፍጣ በወር 200 ሊትር ይመደብለታል፡፡

## ክፍል አራት

8. ለተሽከርካሪ የሚውሉ ግብዓቶች አጠቃቀም፣ አያያዝና ቁጥጥር

8.1 ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት አያያዝ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር

በከተማና በመስክ ጉዞ ላይ የሚወጣወን ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ወጭ ለመቆጣጠርና ለተፈቀደው ሥራ ብቻ መዋሉን ለሚያጋገጥ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

8.1.1 የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ፍጆታ ጥናት በሥምሪትና ጥገና ባለሞያዎች ተዘጋጅቶ በሥራ ሂደቱ ዳይሬክተር ፀድቆ በሠንጠረዥ ይቀመጣል፣

8.1.2 ተሽከርካሪ በግል ለተመደበላቸው የስራ ኃላፊዎች ለከተማ ወስጥ እንቅስቃሴ በሳምንት አንድ ጊዜ የተመደበላቸውን የነዳጅ ኮታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፣

8.1.3 የስምሪት ባለሞያው ለመስክ ጉዞ የተመደበ ተሽከርካሪ የነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት እንዲሁም አነስተኛ ጥገና ወጪዎችን አስልቶ ለጉዞው ቡድን መሪ ወጪእንዲያደረግ ያሳውቃል፣

8.1.4 የመስክ ጉዞ ቡድን መሪው ተሽከርካሪው የሚያስፈልገውን ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት በመስክ ላይ ከሚገኝ ነዳጅ ማደያ በመግዛት ደረሰኝ መቀበል ይኖርበታል፣ በጉዞ ላይ ላጋጠሙ አነስተኛ ጥገናዎች ወጪዎችም በተመሳሳይ መልኩ ደረሰኝ ይቀበላል፣

8.1.5 የቡድን መሪው በመስክ ጉዞ ወቅት ያወጣውን የነዳጅ፣ የዘይትና ቅባት እንዲሁም የጥገና ወጪዎችን ዝርዝር ከአሽከርካሪው ጋር በማረጋገጥ ከመስክ ጉዞ መልስ ሂሳቡን በ7 ቀናት ወስጥ ማወራረድ ይኖርበታል፤

8.1.6 አሽከርካሪው በከተማና በመስክ ጉዞ መጀመሪያና በጉዞው ላይ የተሞላውን ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት እንዲሁም ኪሎ ሜትር በተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ (ባቄሸ ቄቄቀ) ላይ ይመዘግባል፣ የስምሪት ባለሞያውም ሚጃው በትክክል መመዝገቡን ያረጋግጣል፡ ፡

8.1.7 በአንቀጽ 8.1.6 መሰረት ኢንስቲትዩቱ አሰራሩን ወጥ ለማድረግ እንዲያግዘው ሁሉም ተሽከርካሪዎች ጌጅ እንዲኖራቸውየማድረግ ግዴታ አለበት፡ ፡

8.1.8 የስምሪት ባለሞያው የሳምንቱ የተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ፍጆታ ከተጓዙት ኪሎ ሜትር ጋር አገናዝቦ አግባብነቱን በማረጋገጥ ለተሽከርካሪ፤ እርሻመሳሪያዎች ጥገናና ትራንስፖርት ማኔጅመንት ዳይሬክተር ሪፖርት ያቀርባል፡ ፡

## 8.2 የተሽከርካሪዎች መለዋወጫዕቃዎች አቅርቦት፣ አያያዝና አጠቃቀም

8.2.1 በንብረት ክፍል ውስጥ በቂ ክምችት ያለመኖሩ እንዲሁምአግባብ በቂ በጀት መኖሩ ሰረጋገጥ የጠቅላላ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ባትሪ፣ ጎማና የውስጥ ላስቲክ(ከነመዳሪ) ግዥ ጥያቄ በጥገና ባለሙያ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፣

8.2.2 በመስክ ጉዞ ላይ ብልሽት ላጋጠመው ተሽከርካሪ ለሚያጋጥሙ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች እስከ ብር 1=500 ወይም በዓመት ውስጥ እስከ ብር 30=000 ድረስ የሚደረግ ግዥ በመስክ ሰራተኛው እና በሾፌር አማካኝነት ተፈጽሞ ጥገናው ይከናወናል፣ የተለወጡ የመለዋወጫ ዕቃዎችንም አሽከርካሪው በጥንቃቄ ይዞ ለጥገና ክፍሉ ያስረክባል፣ የጥገናውም አግባብነት በጥገናው ባለሙያ ይረጋገጣል፣

8.2.3 የተሽከርካሪ ጥገና ባለሙያው በግዢ የሚቀርቡ የመለዋወጫ ዕቃዎችክፍያ ከሚፈፀሙ በፊት በተጠየቀው መሠረት ጥራታቸው ተጠብቆ መቅረባቸውን ያረጋግጣል፣

8.2.4 ማንኛውም ግዥ ከተመዘገበ አስመጪ ኩባንያ ወይም ዕቃ አቅራቢ መሆን ይኖርበታል፣

8.2.5 በአስመጪ ኩባንያዎች ጋራዥ ውስጥ ከሚከናወን የተሽከርካሪዎች ጥገና በስተቀር፣ በውስጥና በውጪ ጋራዦች ለሚደረግ ጥገና የሚያስፈልግ የመለዋወጫዕቃ ግዥ በዋናው ማዕከል ወይንም በሚከላት ብቻ ይፈጸማል፣

8.2.6 ማናቸውም በግዥ ወይም በእርዳታ ወይም በስጦታ የሚገኙ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎችበንብረት ክምችትና ክፍፍልክፍል ገቢና ወጪ ይደረጋሉ፣

8.2.7 ከንብረትክምችትና ክፍፍልክፍል ወጪ የሆኑ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በዋናው ማዕከልና ሚከላት ጋራዥ የመለዋወጫግምጃ ቤት ገቢ ተደርገው በማጠየቂያ ቅጽ ወጪ እየሆኑ በተሽከርካሪ ላይ እንዲገጠሙ ይደረጋል፣

8.2.8 የጥገና ባለሙያውአዳዲስ መለዋወጫዎች በትክክል በተሽከርካሪው ላይ መገጠማቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

8.2.9 የጥገናባለሙያው ያገለገሉ መለዋወጫዎችንበትክክል መዝግቦ ላገለገሉ መለዋወጫ ዕቃዎች ሚከማቻ መጋዘን በቅጽ አስፈርሞ ያስረክባል፣

8.2.10

ገለገሉ የተሸከርካሪ ጎማዎች እንዲተኩ ሾፌሩ/ተጠቃሚው ሲጠይቅ፣ የጥያቄው ትክክለኛነት በጥገና ባለሙያው ተረጋግጦ የጎማ መተኪያ ቅጽ ይሞላል፣ አሮጌዎቹ ተፈትተው አዳሶቹ ይገጠማሉ፣

8.2.11

ገለገሉ ጎማዎች መጀመሪያ ወጭ ከሆኑበት ቅጽ ጋር የምርት ቁጥራቸው ተገናዝቦ ላገለገሉ ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን ገቢ ይደረጋሉ፣

8.2.12

ዋናው ማቤትና በሜከላት የሚገኙ የተሸከርካሪ መለዋወጫዎችን በትወላት ወይንም በዝወወር ማጠቀም ይቻላል፡ ፡

# ክፍል አምስት

## 9. የኢንስቲትዩቱ ተሸከርካሪ ጥገና

ኢንስቲትዩቱ በዋናው ማቤትና በምርምር ሜከላት የሚገኙ ተሸከርካሪዎች የማቋርጥ የስምሪት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚከተሉት የጥገና አሜራሮችን ይጠቀማል፡ ፡

### 9.1 በወስጥ ጋራዥ የሚከናወን የተሸከርካሪ ጥገና

9.1.1 አሽከርካሪው/ሾፌሩ/ የተሸከርካሪ ጥገና ጥያቄ ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል፣

9.1.2 የጥገና ባለሙያ የጥገና ጥያቄውን ማዘግቦ ይረከባል፣ ይሚምሬል /ይፈትሻል/ ጥገናው እንዲከናወን ያደርጋል፣

9.1.3 የጥገና ባለሙያው መለወጥ የሚባቸው የመለዋወጫ ዕቃዎችን ዝርዝር ከነመለያ ቁጥራቸው (ሓርቂቌ ቃበቂሯስቂ) ያዘጋጃል፣ መለዋወጫው ዕቃ በግምጃ ቤት ወስጥ

መኖሩን በሚጋገጥ ውጭ ያደረጋል፣ ያለመኖሩ ከተረጋገጠ የግዥ ማጠየቂያ ሞልቶ ይጠየቃል፣ የተረከበውንም አዲስ መለዋወጫ ተሽከርካሪው ላይ ይገጥሜል፣

፱.1.4 ጥገናው የተጠናቀቀለት ተሽከርካሪ በጥገና ባለሙያ ተፈትሾ ሲረጋገጥ አሽከርካሪው /ሾፌሩ/ በቀረበው የጥገና ጥያቄ መሠረት ማጠገኑን አረጋግጦ ይረከባል፣

፱.1.5 የጥገና ባለሙያዎች ስለተከናወኑ የጥገና ሥራዎች ከጊዜ፣ ከወጪ ከጥራትና የብልሽቱን ማስኤ በየ 15 ቀኑ በመገምገም ይገመግማሉ፣ ለዳይሬክቶሬቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፣

## ፱.፪. በውጭ ጋራዥ የሚከናወን የተሽከርካሪ ጥገና

### ፱.፪.1 የጥገና አፈጻጸም

የተሽከርካሪው ብልሽት በውስጥ ጋራዥ መከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ በአቅራቢያ ያሉትን ከፍተኛ የጥገና አቅም ያላቸው የግል ጋራዦችን በማግስት መሪያ መሰረት በማወዳደር የሚጠገን ሆኖ፤

- አሽከርካሪው/ሾፌሩ/ የተሽከርካሪ ጥገና ጥያቄ ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል፣
- የቀረበው የተሽከርካሪ ጥገና ጥያቄ በጥገና ባለሙያ ይመረመራል፤ በውጭ ጥገና ማጠገን እንዳለበት ሲታመንበት ባለሙያው የውጭ ጥገና ማጠየቂያና የአገልግሎት ግዥ ማጠየቂያ ይሞላል፣
- የተመረጠው ጋራዥ ለጥገና የሚያስፈልገውን የመለዋወጫ ዕቃ ብዛትና ዓይነት ዝርዝር በጽሑፍ አቅርቦ በዳይሬክቶሬቱ ሲታመንበት የዕቃ ግዥ ማጠየቂያ በጥገና ባለሙያው ተሞልቶ /በትራንስፖርት ተ/ጥ/ዳይሬክተር ተረጋግጦ ግዢው እንዲፈጸም ይደረጋል፣
- የጥገና ባለሙያው የጥገናውን ሂደትና አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፣
- ጥገናው እንደተጠናቀቀ አሽከርካሪውና የጥገና ባለሙያው በጋራ ሆነው በሚቴሽ በጥያቄው መሠረት ጥገናው መከናወኑን ያረጋግጣሉ፣ የጥገና ባለሙያውም ተሽከርካሪውንና ያገለገሉ መለዋወጫዎችን ከጠጋኝ ድርጅት ይረከባል፣

- የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የጥገና ውጤና የብልሽቱ ዓይነት በተሽከርካሪው የሕይወት ታሪክ ላይ በስምሪት ባለሙያው እንዲሞላ፣ የጥገና ባለሙያው በዝርዝር አዘጋጅቶ ያቀርብለታል፣
- በጥገና ባለሙያዎችና በውጭ ጋራዥ የተጠገኑ ተሽከርካሪዎች መግለጫ በየወሩ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ይደረጋል፣

### ፱.፪.፪ የጥገና ኮሚቴ ስለማቋቋም

በውጭ የሚከናወኑ የተሽከርካሪ ጥገናዎችን የሚከታተልና የሚያስፈጽም በዋናው ማቤትና በማእከላት ቁጥራቸው ከ3 ያላነሰና ከ5 ያልበለጠ አባላት ያሉበት ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡ የሚቋቋመው ኮሚቴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

- የውጭ ጥገና በሚያስፈልግበት ወቅት በአስፈላጊነቱ ላይ ተወያይቶ የውሳኔ አስተያየት ለማእከሉ ዳይሬክተር ያቀርባል፣
- የማእከሉ ዳይሬክተር ጥገናው እንዲከናወን ሲያምንበት የማግስትን የግዥ መመሪያ መሰረት በማድረግ የጥገናውን ሂደት በቅርብ ተከታትሎ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡
- ለወድድር የቀረቡትን ጋራጆች ደረጃቸውን፣የፋይናንስ አቅማቸውን፣ የኢንሹራንስ ሽፋናቸውን እንዲሁም ቀደም ሲል የነበራቸውን ሚልካም አፈጻጸም ገምግሞ ደረጃ በማውጣት ለሚመለከተው የሥራ ሂደት ያቀርባል፣
- አሸናፊ በሆነ ወም ድርጅት ብቻ ጥገናው መከናወኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
- በጥገና ሂደቱ ላይ የአፈጻጸም ችግር ካጋጠመ ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር ችግሩ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥረት ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለማእከሉ ዳይሬክተር ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ፱.፫. በተሽከርካሪ አስመጪ ኩባንያዎች /ድርጅቶች/ ጋራዥ ውስጥ ስለማስጠገን፣

- ➢ የዋናው አምራች ኩባንያ ወኪል ጋራጆች /ድርጅቶች/ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቧቸው ተሽከርካሪዎች ብቁ የጥገና ጋራዥና ጥራታቸውን የጠበቁ (ዐሰቃዐሸቃሰ) የመለዋወጫ ዕቃዎች አቅርቦት ያላቸው መሆኑ ሲታመንበት በእነኚሁ ጋራጆች ውስጥ ተሽከርካሪዎች እንዲጠገኑ ይደረጋል፣

፱.፬. በተደራጁ ማኅግሥታዊና ማኅግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋራዥ ውስጥ በትብብር ማስጠገን፣

- ➢ በውስጥ አቅም በግል እንዲሁም በዋና አምራች ከባንያ አስመጪ ጋራዦች ውስጥ ማስጠገን ካልተቻለ በዋናው ማቤቱና በሚከላት አቅራቢያ የተደራጁ ጋራዦች ባሏቸው ማኅግሥታዊና ማኅግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት በማድረግና ማላዋውጫዎችን በማቅረብ የተሽከርካሪ ጥገና እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ፲. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሾፌሮች ተግባርና ኃላፊነት

### ተሽከርካሪ በግል የተፈቀደለት ኃላፊ ተግባርና ሃላፊነት

- ○ በሚያሽከረክርበት ጊዜ የተሰጠውን ልዩ የማሽከርከር ፍቃድ ይይዛል፣ በማንኛውም የህግ አስከባሪ አካል ሲጠየቅ ያሳያል፣ ለሌላ ሰውአሳልፎ መስጠት አይችልም፣
- ○ ተሽከርካሪውንና በውስጡ ያለውን ማልገያ መሣሪያ /ክሪክ፣ መፍቻ፣ ትርፍ ጎማ ...ወዘተ/ ይረከባል፣ ጊዜውን ጠብቆ ሰርቪስ ያስደርጋል፣ ደህንነቱን ይጠብቃል፣ ይንከባከባል፣
- ○ በተሽከርካሪውላይ ለሚደርሰውአደጋ ኃላፊነት አለበት፤ ይህም ማለት በተመደበለት ተሽከርካሪ አደጋ በሚደርስበትጊዜ በትራፊክ ፖሊስ በሚሰጥ ሚጋገጫጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በደንቡ መሠረት የአክሰስ ክፍያይከፍላል፣ አደጋውእንደደረሰም ለትራንስፖርት ስምሪት ባለሙያ ሪፖርት ያደርጋል፣
- ○ ተሽከርካሪ በግል የተመደበለት ኃላፊ ከኃላፊነት ሲነሳ የተረከበውን ልዩ የማሽከርከር ፍቃድ፣ ተሽከርካሪውንና በውስጡ ያሉትንተጓዳኝ መሣሪያዎችን በተረከበው መሠረት ያስረክባል፣
- ○ ከኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች በስተቀር ሌሎች ኃላፊዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን ተገልግለው በማቤቱ ቅጥር ግቢ ሲያቆሙቀጥለውእስከጋለገሉ ድረስ ባለውጊዜ ተሽከርካሪው ለስራከተፈለገበስምሪት ባለሙያ እየተረጋገጠ ተጨማሪአገልግሎትእንዲሰጥ ይደረጋል፣ ለዚሁ ሥራ የወጣውነዳጅ እንዲተካይደረጋል፣
- ○ የማሽከርከር ልዩ ፈቃድ የተሰጠውኃላፊ የተመደበለትን ተሽከርካሪ ከጥገና ባለሙያ በስተቀር ለሌላ ሰውእንዲያሽከረክር መስጠት አይፈቀድለትም፡፡

## ፲.፪. የኢንስቲትዩቱ ሾፌር ተግባርና ሃላፊነት

- ▪ የኢንስቲትዩቱ ንብረት የሆነ ተሽከርካሪን እንዲያሽከረክር ኃላፊነት የተሰጠውሾፌር የራሱንና አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተሳፋሪዎችደህንነት እንዲሁም የአገሪቱን የማንገድ

ትራንስፖርት ህግና ደንብ ከማክበር ባሻገር በባለቤትነት ስሜት በጥንቃቄ የማሽከርከር እንዲሁምተሽከርካሪዉን በእንክብካቤ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡ ፡

- በመሆኑም የሚከተሉትንተግባርና ኃላፊነቶች እንዲሁም የሥነ-ምግባር መርሆዎችንመጠበቅ ይኖርበታል፡ ፡
  - ✓ ሾፌሩ ለሥራ ከመሰማራቱ በፊት ራሱንና ተሽከርካሪውን ለሥራ ዝግጁ ማድረግ፣
  - ✓ ከመጠጥ፣ ከአደንዛዥዕጾና ሰሰኝነት ራስን መጠበቅ፣
  - ✓ የግልና የተሽከርካሪ ንጽህናንመጠበቅ፣
  - ✓ የኢንስቲትዩትን ተሽከርካሪ ከተመደበበት ተግባር ዉጭለሌላ አገልግሎት አለማዋል፣
  - ✓ ለተሽከርካሪው የሚሰጠውን ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት በታማኝነት ለተመደበለት ሥራ ብቻ ማዋል፣
  - ✓ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሰዓት ማክበር፣
  - ✓ በሥራቦታ ወይም በጉዞ ላይ ባጋጣሚ የሚሰማቸውን የመቤቱን ሚስጥሮች መጠበቅ፣
  - ✓ የጥንቃቄ ቀበቶ ማሰርና ተሳፋሪዎች እንዲያስሩ ማድረግ፣
  - ✓ ዘወትር የመንጃ ፈቃዱን መያዝና ማሳደስ፣
- በጉዞ ወቅት ሾፌሩና ረዳቱ የተቋሙሠራተኞች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ /ባጅ/ በደረት ማንጠልጠል አለባቸው፣
- የተሽከርካሪ የዕለት መቆጣጠሪያ ማዘገብ (ሳቄሽ ቄቄቀ) የሚገይቀውን መረጃ በየቀኑ በአግባቡ ማዘግበ በተሽከርካሪው ውስጥ መያዝ፣
- በተሽከርካሪው የዕቃ መጫኛ ሥፍራ ላይ ሰው አለመጫን፣
- በተሽከርካሪ ዉስጥ ተሳፋሪወንም ሆነ አካባቢዉን የሚረብሽ የሙዚቃ ድምፅ አለማሰማት እንዲሁም የእምነት ማዘሙሮችን አለመክፈት፣
- ጽህፎችንና ምስሎችን በተሽከሪካሪው ላይ አለመለጠፍ፣
- ለረዳቱ ተሽከርካሪውን እንዲያሽከረክር አለመፍቀድ፣
- ሞተር ብስክሌት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ እንደሄልሜት ያሉ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን መጠቀም፣
- ከኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን የሥራ ልብስ /ዩኒፎርም በንጽህና ጠብቆ መልበስ፣
- እያሽከረከሩ ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይም ኤርፎን አለመጠቀም፣
- ለሥራ በከተማም ሆነ በመስክ የተሰማሩን ተሽከርካሪ ከበድን መሪወና ከተጠቃሚዎች እውቅና ዉጭወደ ሌላ ቦታ አለማንቀሳቀስ፣
- ከተሽከርካሪው የጭነት ልክ በላይ አለመጫን፣

- ከመኪክ ጉዞ ሜሌስ ተሽከርካሪወኝ አጥቦ፣ አጽድቶና ግሪስ አደርጐ ለሚቀጥለው ስምሪት ዝግጁ ሜድረግ፣
- በሚሽከረከረው ተሽከርካሪ ላይ ስርቆት፣ ብልሽት ወይም አደጋ ቢያጋጥም በአካባቢው ለሚኘ ፖሊስና
- ለማቤቱ የትራንስፖርት ክፍል ኃላፊና ኢንሹራንስ ኦፊሰር ወዲያው ዝርዝር ሪፖርት በስልክ ወይም በጽሁፍ ማቅረብ፣

10.2.23 ከመኪክ ጉዞ ሜሌስ ለቅርብ አለቃው ስለጉዞው በጽሁፍ ሪፖርት ማቅረብ፤ እነ ዚህንና ሌሎችም ከአንድ

መንግሥት ሠራተኛ የሚጠበቁ ተመሳሳይ ሜልካምሥነ-ምግባሮችአሽከርካሪወ/ሾፌሩ/ አክብሮ ለገኘ ይገባል፡፡

10.2.24 አሽከርካሪወ/ሾፌሩ የኢንስቲትዩቱን ተሽከርካሪ በመንግሥት ማቤት ወይንም ለጥበቃ አመቺ በሆነ ቦታ ማስደር አለበት፣

ከሥነ-ምግባር ውጭየሆነ አሽከርካሪ በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 መሠረት ጥፋቱ በዲስፕሊን ኮሚቴ የሚታይ ይሆናል፡፡

## ከተሽከርካሪ ተጠቃሚዎች የሚጠበቁ ስነ ምግባሮች

የኢንስቲትዩቱን ወይም የሚከራዩን ተሽከርካሪ ለከተማ ወስጥና ለመኪክ ሥራዎች እንዲሁም የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎት የሚጠቀም ተገልጋይ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሥነ ምግባሮች እንዲያሟላ ይጠበቃል፡፡

<u>ለከተማ ስምሪት</u>

የተመደበለትን ተሽከርካሪ ለመንግስት ሥራ አገልግሎት ብቻ ማዋል፤

በከተማ ወስጥ ጉዞ ወቅት የሥራ ጊዜን በአግባቡ ማጠቀም፤

ጉዞው ከሌሎች ግለሰቦችና የስራ ሂደቶች ጋር በጣምራ ከሆነ በመግባባት ተሽከርካሪወን ማጠቀም፤

ጊዜንና ጉልበትን ለመቆጠብ፣ የነዳጅ ፍጆታን እንዲሁም ወጪን ለመቀነስ ተሽከርካሪን በጥምር ለማጠቀም ዝግጁ መሆን፤

<u>ለሥራ የሚሄዱበትን አካባቢና ማቤት በቅድሚያ ማወቅ፤</u>

**በመስክ ጉዞ**

- አብረውከሚጓዙት የሥራ ባልደረቦች ጋር ተግባብቶ መጓዝ፤
- የጉዞ መነሻ ሰዓትን አክብሮ በቦታውመገኘት፤
- ተሽከርካሪ የሚመደበው ጉዞው ለተፈቀደለት ሰው ብቻ መሆኑን ጠንቅቆ በማወቅ አስፈላጊውን ሚፈጸም፤
- የተመደበውን ተሽከርካሪ ጤንነትና ንጽህና ማጠበቅ፤
- በጉዞ ላይ የሌሎች በድን አባላትን መብት ማክበር፤
- ለጉዞ የተፈቀደውን ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም ወደ መደበኛ የሥራ ቦታ መመለስ፤

**በከተማ ውስጥ ትራንስፖርት ሰርቪስ**

- የትራንስፖርት ሰርቪስ ተጠቃሚ በሰርቪስ ተሽከርካሪ ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት ቁሻሻ ባለመጣል የተሽከርካሪውን ንጽህና የማጠበቅ፤
- ተጠቃሚው በየፈርማቸው የተመደበውን የመነፈሪያ ሰዓት አክብሮ መገኘት፤
- የትራንስፖርት ሰርቪስ ተሽከርካሪ ከዋናው ማቤት/ከሜከል መነሻ ሰዓትን አክብሮ በመነፈሪያው ቦታ መገኘት፤
- የትራንስፖርት ሰርቪስ ተሽከርካሪ ላይ የሌላውን ተጠቃሚ ምቾት የሚነሱ ድርጊቶች አለሚፈጸም፤
- እያንዳንዱ ተጠቃሚ የግል ንጽህናውን ማጠበቅ ይኖርበታል፤
- በትራንስፖርት ሰርቪስ ተሽከርካሪ ላይ ያሉትን ቁሳቁሶች በአግባቡ ማጠቀም፤

# <u>ክፍል ሰባት</u>

**11.**

**11.1**

በማንኛውም የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ ላይ የሚደርስ አደጋ ኢንስቲትዩቱ በገባው ዉል መሰረት

የሚደህን ሽፋን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**11.2**

የትራንስፖርት ስምሪት በኢንስቲትዩቱ የታቀዱ የምርምር ሥራዎችን በሚለገው ማበና ጥራትበአጭር ጊዜእንዲሰኩ ከሚደርገው ያላሰለሰ ጥረት ጐን ለጐን በኢንስቲትዩቱ ዋናው ማቤትና በሚከላት ሠራተኞች፣ ወርክሾፖች ወስጥና በተሽከርካሪዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱት ተግባራት መከናወን አለባቸው፡

11.2.1 በኢንስቲትዩቱ ዋናው ማቤትና በሚከላት በሚገኙ ወርክሾፖች ወስጥና በተሽከርካሪዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል የሚዱ መሣሪያዎችንና የእሳት ማጥፊያዎችን በየጊዜው ጥራታቸዉና የአገልግሎት ጊዜያቸው እየታየ እንዲታደሱና እንዲስተካከሉ በሚደረግና አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች በማስቀመጥ አደጋውን ለመከላከል እንዲያስችሉ ዝግጁ ማድረግ፣

11.2.2 የእሳት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ አደጋዎች ቢያጋጥሙ ሠራተኞች ሳይደናገጡ አደጋውን በቁጥጥር ሥር ሊያዉሉስለሚችሉበት ሁኔታና ስለ እሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ለጥገና ባለሞዎች፣ ለአሽከርካሪዎች፣ ለጥበቃ ሠራተኞች.. ወዘተ ሥልጠና መስጠት፣

11.2.3 በኤሌክትሪክ በሚሽከረከሩ መሣሪያዎች፣ በብረታ ብረት ብየዳና ቅጥቀጣ እንዲሁም በቀለም ቅብ ወቅት የተለያዩ አደጋዎች ሊደርሱ ስለሚችሉ፣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣

11.2.4 በእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ላይ የእሳት አደጋ መከላከያ እንዲገጠም ማድረግና ማጠቀም፡

## ክፍል ሰምንት

## ፲፪. ስለ ሪፖርት አቀራረብ

፲፪.1

ኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ ሁሉም የምርምር ማዕከላት በተሽከርካሪ ስምሪትአጠቃቀም ላይ የተከናወኑ ተግባራትን ያጠቃለለ ግልጽና ተጨባጭ የሆነ ወርሃዊ ሪፖርት በሚመከሉ ዳይሬክተር ተረጋግጦ ወር በገባ እስከ ፭ኛው ቀን ለኢንስቲትዩቱ ትራ/ተ/እ/ማጥ ዳይሬክቶሬት መድረስ አለበት፡ ፡

፲፪.፪

የኢንስቲትዩቱ ትራ/ተ/እ/ማጥ ዳይሬክቶሬትም የማዕከላቱንና የዋናውን ማዕከል ወርሃዊ ሪፖርት በማጠናቀር ለኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር ያቀርባል እንዲሁም ለሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ይልካል፡ ፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ

፲፫.

- የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪ፤ መለዋወጫ ባትሪና ጎማ አወጋገድን በተመለከተ በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ፱/፪003 ላይ ስለ መንግስትንብረት አስተዳደርና አወጋገድ የሚደነግጉ አንቀፆች በሥራ ላይ ያሉት የመንግስት የቋሚንብረት አስተዳደር እና የስቶክ አስተዳደር ማንዋሎች እንደአግባብነታቸው ለኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡ ፡
- የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሂደቶችና ማዕከላት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የሆኑትን ቅፆች መጠቀም አለባቸው፡ ፡

➢ አገልግሎታቸውን የጨረሱ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በማግስት የንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

14. ጾታዊ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጹት ሁሉ ለሴት ጾታም ያገለግላሉ፡፡

15. የተሻረ መመሪያ እንዲሁም ሰርኩላሮች

ቀደም 1978 ዓ.ም በኢንስቲትዩቱ የወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት መመሪያ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን የተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም ለማሻሻል በተለያየ ጊዜ ከኢንስቲትዩቱ የተላለፉ ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

16. መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ በላይ ኃላፊ ከፀደቀበት ከዛሬ ሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**መመሪያውን ያጸደቀው የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር**

ስም፡ ______________________ ፊርማ __________ ቀን፡ ______________________